ክፋት ለምን ተፈቀደ? እንዴት ተጀመረ? መጨረሻውስ?

ከዘላለም እስከ ዘላለም እግዚአብሔር ፍቅር ነው

ክፋት

እንዴት ተጀመረ?
ለምን እስካሁን ቆየ?
እንዴት ይጠናቀቃል?

ክፍል 2

አጀንዳ

- ክፍል 1፡ ክፋት በማን እና እንዴት ተጀመረ?
- ክፍል 2፡ እግዚአብሔር ለምን ወዲያውኑ አላጠፋውም?
- ክፍል 3፡ በሰማይና በምድር ላይ የሆነው ጦርነት
- ክፍል 4፡ ዘመናዊው የክፋት ስትራቴጂ
- ክፍል 5፡ የክፋት መጨረሻ

ሉሲፈር ማን ነበር?

- የስሙ መነሻ — ኢሳይያስ 14:12
  - ዕብራይስጥ፡ *hêlēl ben-shāchar* — “የማለዳ ልጅ፣ አብሪው ወይም አንጸባራቂው” ("Shining or brilliant one, son of dawn.")
  - ግሪክ፡ *heōsphoros* — “ብሩህ ኮከብ፣ ንጋት አብሳሪ” ("Bright one, morning star.")
  - ላቲን / እንግሊዘኛ፡ Lucifer — “ብርሃን ተሸካሚ” ("Light-bearer.")
- መሠረታዊው መመሪያ፡
  - የተፈጠረው የእግዚአብሔርን ብርሃን እንዲሸከም እና እንዲያንጸባርቅ እንጂ፣ እርሱ ራሱ የብርሃኑ ምንጭ አልነበረም
  - “አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ” (ሕዝ. 28:14)

ሉሲፈር ከውድቀቱ በፊት የነበረው የክብር ደረጃ

- ከፍተኛው የፍጥረት ደረጃ፡
  - ከእግዚአብሔር ልጅ ቀጥሎ ታላቅ ክብር የነበረው፣ የተከበረ ከፍተኛ መልአክ ነበረ
- በሁሉም ረገድ ፍጹም ነበር፡
  - ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ (ሕዝ. 28፡12)
  - የላቀ አዕምሮ (Intellect) እና powerful reasoning capabilities ነበረው
  - የሥራ ድርሻ (Position)፡ “አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ ነበርህ፤ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ አኖርሁህ፤ በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ በእግዚአብሔር ቅዱስ ተራራ ላይ የተቀባ የሚጋርድ ኪሩብ ነበረ” (ሕዝ. 28:14)
- ውጫዊ ገጽታ (Appearance)፡ ከሌሎች መላእክት ሁሉ ይልቅ የሚበልጥና የሚያምር ብርሃን ያንጸባርቅ ነበር (1SP 17.1)

ክፋት እንዴት ተጀመረ?

- እንከን የለሽ ፍጥረት፦
  - “ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ” (ሕዝቅኤል 28:15)
- የጥበብ መበላሸት (The Corruption of Wisdom)፦
  - “በውበትህ ምክንያት ልብህ ታብዮአል፥ ከክብርህም የተነሣ ጥበብህን አበላሽተሃል” (ሕዝቅኤል 28:17)
- የክፋት ብልጭታ (The Spark of Evil)፦
  - ኃጢአት የተከሰተው ከውጭ በመጣ ፈተና (external temptation) ሳይሆን፥ በራስ ወዳድነት፥ በኩራት፥ በተበላሸ ጥበብ ምክንያት ከውስጡ የፈለቀ ነው
  - “እንተም በልብህ” (ኢሳ. 14፡13)

የጥበብ መበላሸት

ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አንዋዋረ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ። ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው፤ ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፋ ስራ ሁሉ አሉና። ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ (ሰላም ወዳድ)፥ ገር (ታጋሽ)፥ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት። የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል። (ያዕቆብ 3፡13-18)

ራሰን አምላክ የማድረግ ውቅር

- The Five "I Wills" of Lucifer፦
  - “ወደ ሰማይ እወጣለሁ…” ("I will ascend into heaven...")
  - “ዙፋኔን ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ…” ("I will exalt my throne above the stars of God...")
  - “በጉባኤ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ…” ("I will sit on the mount of the congregation")
  - “ከደመናዎች ከፍታ በላይ እወጣለሁ” ("I will ascend above the heights of the clouds")
  - “በልዑልም እመሰላለሁ” (ኢሳይያስ 14:13-14) ("I will be like the Most High.")
- የኃጢአት ዋናው መዋቅር፦
  - ራስን በዙፋን ላይ ለመቀመጥ ሲባል ፈጣሪን ከቦታው ለመንቀል መሞከር
  - “በንግድህ ብዛት ግፍ በውስጥህ ተሞላ … በበደልህ ብዛት በንግድህም ኃጢአት መቅደስህን አረከስህ” ሕዝ. 28፡16፣18

ከሉሲፈር ወደ ሰይጣን የተደረገ ሽግግር

- ከ“ብርሃን ተሸካሚ” ወደ “ባላጋራ” (Adversary)
  - ሰይጣን (ዕብራይስጥ)፦ ከሳሽ፣ ጠላት ወይም ተቃዋሚ (accuser, adversary, or opponent) ማለት ነው
  - ዲያብሎስ (ግሪክ)፦ ስም አጥፊ ወይም ሐሜተኛ (slanderer) ማለት ነው
- የተለወጠው ማንነቱ፦
  - የከሚጋርድ ኪሩብነት “ከመጀመሪያ ጀምሮ ነፍሰ ገዳይ” ወደ መባል ተለወጠ
  - “እውነትም በእርሱ” የሌለበት “በእውነት አልቆመም”
  - ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤
  - “ሐሰተኛ የሐሰትም አባት” (ዮሐንስ 8:44)

እግዚአብሔር ለምን ወዲያውኑ አላጠፋውም?

- የሁሉን ቻይነት ወሰን — The Limits of Omnipotence
  - እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ (all-powerful) ከሆነ፣ ለምን ሰይጣንን ወዲያውኑ አክስሞ (instantly vaporize) ኃጢአትን ከሥሩ አላስቀረውም?
- የማይቃረን እውነት መርህ (The Principle of Non-Contradiction)፦
  - ሁሉን ቻይነት (Omnipotence) ማለት እግዚአብሔር ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ማድረግ ይችላል ማለት ነው፤ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አመክንዮዎችን (logical contradictions) አያደርግም
  - እግዚአብሔር ነፃ ፍጡርን እንዲወደው አያስገድድም
  - ምክንያቱም የተገደደ ፍቅር፣ ፍቅር ሊሆን አይችልም (forced love is a logical impossibility) ነው

ሁለቱ ፈቃዶች - Ideal Will vs. Remedial Will

- ፍጹም ፈቃድ (Ideal Will)፦
  - የእግዚአብሔር የመጀመሪያውና ፍጹሙ የፍጥረተ ዓለም ዕቅድ
  - ሙሉ በሙሉ ያልተገደደ፣ እውነተኛ ፍቅርና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው
- መፍትሔ ሰጪ ፈቃድ (Remedial Will)፦
  - ነፃ ፍጡራን ለማመፅ ሲመርጡ፣ እግዚአብሔር ሁለተኛውን “የመፍትሔ” ዕቅድ (remedial plan)
  - ኃይልን ከመጠቀም ይልቅ (ይህ ፍቅርን የሚያጠፋና መላእክትን ወደ ፈሪና ወደ ሮቦትነት የሚቀይር ስለሆነ)፣ እግዚአብሔር በሕጋዊ እና በፍጥረተ ዓለም በሚያየው መልኩ በማሳየት (legal, cosmic demonstration) ለማረጋገጥ የሄደበት መንገድ

ፍጹም ፈቃድ (God's Ideal Will)

- ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ
  - God "works all things according to the counsel of His will" (ኤፌ. 1:11)
- ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው (1ጢሞ. 2:3-4)
- ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ (2. ጴጥ 3:9)
- እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም (ሕዝ. 33:11)
- ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና (ቲቶ 2:11)

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁልጊዜ አይፈጸምም

- ሕዝቤ ግን ቃሌን አልሰሙኝም፥ እስራኤልም አላደመጠኝም (መዝ.81:11)
- ሕዝቤስ ሰምቶኝ ቢሆን፥ እስራኤልም በመንገዴ ሄደው ቢሆን፤ ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባዋረድኋቸው ነበር፥ በሚያስጨንቁቸውም ላይ እጄን በጣልሁ ነበር (መዝሙር 81:13–14)
- ያልወደድሁትንም መረጡ እንጂ በጠራሁ ጊዜ አልመለሱልኝምና፥ በተናገርሁም ጊዜ አልሰሙኝምና (ኢሳይያስ 66:4)
- በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ፤ በጸጥታና በመታመን ኀይል ይሆንላችኋል፤ እናንተም እንቢ አላችሁ (ኢሳይያስ 30:15)

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁልጊዜ አይፈጸምም

- ታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ ሊመጡም አልወደዱም (ማቴዎስ 22:3)
- ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች ግን በእርሱ ስለ አልተጠመቁ የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ (አቃለሉ) (ሉቃስ 7:30)
- ደሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም (ሉቃስ 13:34)
- ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም (ዮሐንስ 5:40
  - እናንተ ግን፣ ሕይወት እንዲኖራችሁ ወደ እኔ መምጣት አትፈልጉም (አመት)

የተጋድሎው የውጊያ ደንቦች The Cosmic Rules of Engagement

- አስገዳጁ ማዕቀፍ (The Binding Framework)፦
  - እግዚአብሔር በፍቅርና በፍትሕ ስለሚገዛ፣ ራሱን ጥብቅ ከሆኑ “የውጊያ ደንቦች” (Rules of Engagement) ጋር አስተሳስሮአል
- የባሕርይ መገለጫ ተጋድሎ፦
  - ግጭቱ በጉልበት ማሳያ ሳይሆን የሐሳብ ስለሆነ፣ በባሕርይ ማሳያ መፈታት አለበት
  - ሰይጣን በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ የሰነዘራቸው ክሶች ዕድል ተሰጥቷቸው እንዲታዩ መደረግ ነበረበት፤
  - ይህ ካልሆነ የኒቨርስ የዓመፅን አስከፊና ገዳይ ውጤት ማየት አይችልም
  - ለዚህ ደግሞ ጊዜ ያስፈልጋል

ውጊያው ወደ ምድር ዞረ

- በዔድን ገነት የነበረው ወጥመድ
  - የሰው ልጅ ነፃ ፈቃድ ተሰጥቶት ተፈተነ፣ ተሸነፈም፤ በዚህም የምድርን ግዛት ለቀማኛው አሳልፎ ሰጠ (ዘፍጥረት 3)
- የመጀመሪያው የወንጌል ጦርነት አዋጅ
  - “በአንተ (በእባቡ ዲያቢሎስ፣ ሰይጣን) እና በሴቲቱ (ሔዋን፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ) መካከል፥ በዘርህ (የእባቡ ተከታዮችና አስፈጻሚዎች) እና በዘርዋም (የእግዚአብሔር ሐሳብ ተከታዮች) መካከል ጠላትነትን (ተጋድሎ፣ ውጊያ፣ ውዝግብ) አደርጋለሁ…” (ዘፍጥረት 3፡15)
- የመፍትሔው የተስፋ ቃል
  - “እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ” (ዘፍ. 3፡15)
  - የውጊያው አውድማ (battleground) በይፋ ወደ ሰው ልጅ ታሪክ ተዛወረ

የውጊያ ደንቦች በተግባር The Rules of Engagement in Real Time

- የሰማይ ጉባኤ/ስብሰባ
  - ሰይጣን በእግዚአብሔር ልጆች ጉባኤ መካከል በመገኘት ምድርን እንደሚወክል ተናገረ (“በምድር ላይ ተመላለስሁባት” ኢዮብ 1:6-7)
- በሕግ የተቀመጡ ወሰኖች
  - እግዚአብሔር ሰይጣን የኢዮብን ታማኝነት እንዲፈትን ፈቀደለት፣ ነገር ግን ጥብቅ የሕግ ወሰን አገደበት፦ “እነሆ፣ ለእርሱ ያለው ሁሉ በእጅህ ነው፣ ነገር ግን በአካሉ ላይ እጅህን አትዘርጋ” (ኢዮብ 1:12)
  - እግዚአብሔር ውጊያውን የሚመራው በዩኒቨርስ ሕግና ወሰን (cosmic law and boundaries) ነው
  - ይህ ደግሞ ሰይጣን ያልተገደበ ኃይል (unchecked power) እንደሌለው ያረጋግጣል
  - ዳንኤል 10

አሁን ያለንበት እውነታ ባሕርይ

- የሁለት አቻዎች ተጋድሎ አይደለም
  - ይህ የጽንፈ ዓለም ውጊያ በሁለት እኩል ኃይሎች መካከል የሚደረግ ፍልሚያ አይደለም (Yin-Yang)
  - ማቆሚያ የሌለው/ዘላለማዊ አይደለም
- እውነተኛው ውጊያ (The Real Warfare)፦
  - ሰይጣን <u>የተሸነፈና የተገደበ ጠላት ነው</u>
  - እኛ ያለነው በሁለቱ መካከለኛ የተከለ ቀጠና ውስጥ ነው
- “መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር...” (ኤፌሶን 6፡12




በምድረ በዳ፡- የአቋራጭ መንገድ ስትራቴጂ

- የድብቅ/የተሸሸገ ጥቃት (The Disguised Attack)፡
  - ሰይጣን ወደ ክርስቶስ የቀረበው ውብና ብሩህ የብርሃን መልአክ በመምሰል ነበር
  - የወደቀ ፍጡር ሳይሆን የሰማይ ገዥ (celestial monarch) መስሎ ነው
- ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ መሣሪያ መጠቀም
  - The Weaponization of Scripture
  - የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መሣሪያ በመጠቀም “ተጽፎአል…” እያለ ተከራከረ
- ዋናው ፈተና
  - ክርስቶስ መስቀሉን ትቶ የምድርን መንግሥታት ወዲያውኑ እንዲወስድ ሕመም የሌለበት አቋራጭ መንገድ አቀረበለት
  - “ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ” (ማቴዎስ 4:9)

ዘመናዊ ሰትራቴጂ

- የክፋትን ማንነት ረቂቅ ማድረግ
  - በአሁኑ ገዜ በፍጥነት እየተስፋፋ ያለው ስህተት ሰይጣን እውነተኛ አካል ያለው ፍጡር (literal, personal being) አይደለም ብሎ ማመን ነው
  - ተንኮለኛ/ብልህ/ብልጥ - ዘፍ. 3:1፣ ምሳሌ፤12:16, 12:23, 13:16, 14:8, 14:15, 14:18, 22:3, 27:12
  - እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ሉቃስ 10:18-19
- እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራልና፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና። ዮሐንስ 8:44
- “ሰይጣን” የሚለው ስም የሰውን ክፋ ሃሳብና ምኞት የሚወክል ምሳሌያዊ አነጋገር ብቻ ነው ለማለት ቅዱሳን መጻሕፍት በተሳሳተ መንገድ ይተረጎማሉ (GC 524.3)

Christian Views on the Existence of Satan



https://www.barna.com/research/most-american-christians-do-not-believe-that-satan-or-the-holy-spirit-exist/

ዘመናዊ ሰትራቴጂ Pop Culture



- «Lucifer» በተሰኘው ተከታታይ ፊልም ሚካኤል እና ሉሲፈር መንታ
- ሉሲፈር (Lucifer Morningstar):
  - የሲኦልን ዙፋን ትቶ በሎስ አንጀለስ የምሽት ክለብ በመክፈትና ከፖሊስ ጋር በመተባበር የወንጀል ምርመራ የሚያካሂድ ሕይወትና መዳንን የሚፈልግ ገጸ-ባህሪ ነው
- ሚካኤል:
  - በሉሲፈር ላይ በቅናት የተሞላ፣ የሉሲፈርን ምድራዊ ሕይወት፣ ወዳጆችና በሰማያዊ ቤተሰቡ ዘንድ ያለውን ቦታ ለመንጠቅ ወደ ሎስ አንጀለስ የመጣ ተንኮለኛ ሊቀ-መላክ
- ባህርይ:
  - ሉሲፈር: ማራኪ፣ እውነተኛና የሰዎችን የውስጥ ፍላጎት የማውጣት ኃይል ያለው
  - ሚካኤል: አታላይ፣ የሰዎችን የውስጥ ፍርሃትና ስጋት የሚጠቀም ተንኮለኛ
- የሰማያዊ ዙፋን ሽሚያ:
  - በሁለቱ መካከል ያለው የቆየ ውድድርና ጥላቻ የአባታቸውን (የአምላክን) ዙፋን ለመረከብ የሚደረግ ከባድ ፍልሚያ

በመሰቀል ላይ የተገኘው ድል

- የመቀልበሻ ነጥብ
  - ክርስቶስ አቋራጭ መንገዶችን ሁሉ እምቢ አለ፣ መስቀልን ታገሰ፣
- የሰይጣን ጭንብል በሕግ መውለቅ (Satan Legally Unmasked)፦
  - “አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሷል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል።” (ዮሐንስ 12፡31)
- ያልወደቀው ዓለም ደኅንነት ተረጋገጠ
- ንጹሑን የእግዚአብሔርን ልጅ በመግደል
  - ሰይጣን ነፍሰ ገዳይነቱን ላልወደቁት የሰማይ ፍጥረታት (unfallen universe) ሙሉ በሙሉ ገለጠ
- በዚህም ለእርሱ የነበራቸውን ሐዘኔታ (sympathy) ለዘለቄታው አጠፋ

ክፋት ለምን እሰካሁን ቆየ?

ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፦ መንግሥተ ሰማያት በእርሻው መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች። ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ። ስንዴውም በበቀለና በአፈራ ጊዜ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ። የባለቤቱም ባሮች ቀርበው፦ ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት። እርሱም፦ ጠላት (ፀራዊ) ይህን አደረገ አላቸው። ባሮቹም፦ እንግዲህ ሄደን ብንለቅመው ትወዳለህን? አሉት። እርሱ ግን፦ እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም። ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆችን፦ እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነደው እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ። (ማቴዎስ 13:24-30)

ክፋት ለምን እሰካሁን ቆየ?

- የስንዴውና የእንክርዳዱ ምሳሌ (ማቴዎስ 13:24-30)፦
  - አገልጋዮቹ ጠየቁ፦ “ሄደን እንክርዳዱን እንድንሰበስብ ትወዳለህን?”
- ጌታው መለሰ፦
  - “እንክርዳዱን ስትሰበስቡ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትንቅሉ አይሆንም። ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ”
- የመብሰል መርህ (The Maturity Principle)፦
  - ክፋት ሙሉ በሙሉ እንዲበስል (fully mature) መፈቀድ አለበት፤ ይህ ካልሆነ አስከፊና መርዛማ ፍሬው (horrific, natural fruit) በሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ዘንድ በግልጽ ሊታይ አይችልም

የመጨረሻው መፍትሔ፦ የሺ ዓመቱ ማብቂያ


- የመጨረሻው ከበባ፦
  - በሺው ዓመት መጨረሻ፣ ሰይጣን ቅድስቲቱን የእግዚአብሔርን ከተማ ለመውረር የመጨረሻውን የዓመፅ ሙከራ ያደራጃል (ራዕይ 20:7-9)
- የፍጥረተ ዓለሙ የመጨረሻ ፍርድ (The Universal Verdict)፦
  - እያንዳንዱ ፍጡር ስለ እግዚአብሔር ፍጹም ፍትሕ (perfect justice) እና ስለ ሰይጣን የማይለወጥ ክፋ ባሕርይ (unchangeable malice) እውነተኛውን ሐቅ በመጨረሻ ያያል።

በእሳት ሙሉ በሙሉ መጥፋት

- የፍትሕ ፍጻሜ (The Execution of Remedial Justice)፦
  - እሳት ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ ወርዳ ዓመፀኞቹን ትበላለች
- ፍጹም መጥፋት፦
  - “ሰይጣን በሚያየት ሁሉ ፊት በምድር ላይ አመድ ይሆናል” (ሕዝቅኤል 28:18)
  - ለዘለዓለም ወደ እሳት ባሕር ውስጥ ይጣላል
  - ከህያዋን ተለይቶ ይጠፋል፣ ከእንግዲህ ወዲህም አይገኝም
  - “ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው” (ራዕይ 20፡14)

የጸዳ ፍጥረተ ዓለም

- የዘለዓለም ፍርድ (The Eternal Verdict)፦
  - “ታላቁ ተጋድሎ፣ ታላቁ ውዝግብ አበቃ። ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአትና ኃጢአተኞች የሉም። መላው ፍጥረተ ዓለም ንጹሕ ሆነ። ... ከደቂቁ አቶም እስከ ታላቁ ዓለም፤ ሁሉም ሕይወት ያላቸው ፍጡራንና ሕይወት የሌላቸው ግዑዛን በሙሉ፥ ባልተጋረደ ውበታቸው እና ፍጹም በሆነ ደስታቸው እንዲህ በማለት ያውጃሉ፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነው! (GC 678)
- የዩኒቨርስ ምስክርነት (Cosmic Vindication)፦
  - “ፍርድህ እውነተኛና ቅን ነው” (ራዕይ 16:7)
    - ("True and righteous are Your judgments.")
  - የእግዚአብሔር የፍቅር ባሕርይ ለዘለዓለም የተጠበቀና የተረጋገጠ ሆኖ ይኖራል።



በመጨረሻ የሚፈረድለት አምላክ

- The great controversy is ended. Sin and sinners are no more. The entire universe is clean. One pulse of harmony and gladness beats through the vast creation. From Him who created all, flow life and light and gladness, throughout the realms of illimitable space. From the minutest atom to the greatest world, all things, animate and inanimate, in their unshadowed beauty and perfect joy, declare that God is love. (GC 678)
- አዎን፥ ሁኑን የሞትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ። ራዕይ 16:7
- ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ናቸውና ማዳንና ክብር ኀይልም የአምላካችን ነው፤ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም (ራዕይ 19:2፣11)
- እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ለዘላለም ይፈረድለታል!

Further Study

- ማቴዎስ 13:24-30፣ ዘፍጥረት 3፣ ኢዮብ 1-3፣ ኢሳይያስ 14፣ ሕዝቅኤል 28፣ የሐንስ 8:44፣ ራዕይ 12፣ ራዕይ 21-22
- Ellen G. White Writings:
  - Patriarchs and Prophets – Chapter 1: Why was Sin Permitted?
  - The Great Controversy – Chapter 29: The Origin of Evil
  - The Great Controversy – Chapter 30: Enmity Between Man and Satan